# የ፳፻፪ቱ (የኹለት ሺህ ኹለቱ) ዓመተ ምሕረት፣
# የ"ጾመ ኢትዮጵያ" እና የ"ሰላም-ለኢትዮጵያ ጾም"
# ምሕላዎቻችን፣
# <u>ምን ዓይነት ውጤትን አስገኙ?</u>

**ይድረስ፡-** *በ፳፻፪ቱ (በሃያ መቶ ኹለቱ=፪ሺ፪ቱ) ዓመተ ምሕረት አኩሌታ (ከጥር ፲፯-፲፱ ቀን) እና መጨረሻ ላይ (ከጳጉሜ ፩-፫ ቀን) ያካኼድናቸውን፡ የ“ጾመ ኢትዮጵያ”ን እና የ"ሰላም ለኢትዮጵያ ጾም"ን ጥሪዎችና መልእክታት ተቀብላችሁ፡ በእነዚያ ምሕላዎች ለተካፈላችሁ፡ በኢትዮጵያ ላላችሁትና በመላው ዓለም ለተበተናችሁ ኹሉ!*

በአምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በእናታችንና እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም፡ እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ “በያላችሁበት፡ እንዴት ናችሁ?” እያልሁ፡ በኢትዮጵያዊው ወግ፡ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ።

በቀደሙት ዓመታት እንዳደረግነው ኹሉ፡ ያለፈውንም ዘመን፡ የእናት አገራችንን ጥሪዎች ሰምተንና መልእክቶቿን ተቀብለን፡ የምሕላዎቹን ሥርዓት፡ በያለንበት፡ በአግባቡ የፈጸምነውን፡ የእግዚአብሔር ወገኖች ኹሉ፡ “እንኳን ደስ አለን!” እላለሁ።

ይህን ያልሁት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ከአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር፥ ይልቁንም፡ እንደመንግሥታችን ሥርዓት፡ የአገሩ ርእሰ ብሔር፥ ወይም የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱ፥ ወይም፡ የቤተ ምልክናው መሪ ከኾነው ጋር፡ በቀጥሮ ተገናኝቶ፥ ችግሩን፡ በጽሙና አመልክቶና በቆይታ ተወያይቶ፡ ከቤተ መንግሥት የሚወጣ፡ አንድ የተቸገረ፥ ወይም የተበደለ ዜጋ፡ አቤቱታው፡ ወዲያው ባይፈጸምለት እንኳ፡ ይህን የመሰለውን አቀባበልና የመደመጥ ዕድልን በማግኘቱ ብቻ፡ በፊቱ ላይ የደስታና የእርካታ ፈገግታ እየታየበት፡ ወደቤቱ እንደሚመለስ የታወቀ ነው።

ለሦስትና ለአምስት ቀናት፡ ከፈጣሪ እና ከቅድስት እናቱ ጋር፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስም ተገናኝቶ፥ ተወያይቶና ረክቶ መመለስማ፡ እንዴታ፡ በበለጠ አያስደስት!? አዎን! በእጅጉ ያስደስታል።

ከእግዚአብሔር በታደልነው፡ የመምረጥ ነጻነታችንና የመወሰን ሥልጣናችን ተጠቅመን፡ ገናናውን የኢትዮጵያን ስም በማንገብ፡ የእርሱንና የቅድስት እናቱን ፈቃድና ሥርዓት የተከተሉትን፡ እነዚያን ኹለት አጽዋማት፡ በሃይማኖታዊ ምግባር፡ እንዲህ አድርገን፡ ለማከናወን ከበቃን፡ እነዚያው አጽዋማት ስላስገኙት ፍሬ፡ ባለፉት ዘመናት፡ ያዘጋጀሁትን የተለየ መግለጫ፡ እንደገና፡ በማስተዋል ትመለከቱት ዘንድ፡ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቤላችኋለሁ፡-

መግለጫዬን፡ እንዲህ በሚሉ ጥያቄዎች እጀምረዋለሁ፡-

፩. "'በጾመ ኢትዮጵያችን እና በሰላም ለኢትዮጵያ ጾማችን አካኺደን የፈጸምነው፡ ሃይማኖታዊ ምግባራችን፡ ምን ዓይነት ውጤትን አስገኘ?' ለሚለው ጥያቄ፡ መልስ ሊሰጥ የሚገባው፡ ማነው?

፪. እያንዳንዳችን፡ ጥሪዎቹን ሰምተንና መልእክቶቹን ተቀብለን፡ እውን ያደረግነው፡ ያለማንም ተጽዕኖና ያለምንም ግዴታ፡ በየግል ፈቃዳችን፡ እኛው፡ እየራሳችን እንደመኾናችን መጠን፡ ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ መስጠት ያለብንም፡ እኛው፡ እየራሳችን መኾናችንን፡ ኅሊናችን የሚነግረን አይደለምን?

፫. እናት አገራችን ኢትዮጵያ፡ በእነዚያ ጥሪዎቿና መልእክቶቿ፡ ለእኛ፡ ለእያንዳንዳችን፡ የሰጠችውን መመሪያ ተከትለን፡ ከእኛ የጠበቀችውን የንስሓ ፍሬ በማበርከት፡ ግብዣዋን ተሳተፍንላትወይ?"

ወገኖቼ ሆይ! እነዚያ ኹለት የተለዩ፡ የምሕላ አጽዋማት ያስገኙት ውጤት፥ ፍሬያቸውም፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በውስጣችን ያለው፡ የመንፈስ ቅዱስ እውቀት ስለሚያሳስበን፡ ያ ይበቃናል፤ ይህም፡ በእነዚያ፡ በሦስቷና በአምስቷ ቀኖች ውስጥ፡ እያንዳንዳችን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ከፈጣሪያችንና ከቅድስት እናቱ ጋር፡ በጾምና በጸሎት ተጠምደን በፈጸምነው፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኳችን አማካይነት፡ በየግላችን ተገናኝተንና ተነጋግረን ያገኘነው እውቀት ነው።

እርሱንም፡ "ይህ ነው፥ ወይም፡ ይህን ይመስላል!" ብለን፡ አንዳችን ለአንዳችን ለማስረዳት፥ በአጠቃላይም፡ ስለእነዚያ አጽዋማት፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ዜናውን ለመናገር፡ ለእኛ ለተሳታፊዎቹም እንኳ ቢኾን፡ ለማነኛችንም፡ ከዓቅማችንና ከመብታችን በላይ ይኾንብናል።

ምክንያቱ፡ ግልጽ ነው፤ የምንነጋገርበትና የተያያዝነው ጉዳይ፡ የሰው ግምገማና አስተያየት ሊታከልበት የሚቻል ሳይኾን፡ ከዚያ እጅግ የላቀውና የረቀቀው፥ የጠለቀውና የመጠቀው፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር የኾነው ጉዳይ ስለኾነ ነው:: እንዲህ ከኾነ፡ ይህን ጉዳያችንን፡ ሌላ የሚቀድመው ያለ በማስመሰል፡ እንደኹለተኛ ጉዳይ አድርገን፥ ወይም፡ እንደተራ ነገር ቆጥረን፥ በቀላሉም ወስደን፡ ልንመለከተው አይገባም ማለት ነው::

ነገር ግን፡ የክፉው መንፈስና የእርሱ አገልጋዮች የኾኑት ወገኖች፥ ዓለሙና ሥጋችን ጭምር የሚጥሩት፡ ከዚህ፡ የተረጋገጠ አቋማችን ሊያነዋውጹን መኾኑን፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ ቢኾን መዘንጋት የለብንም::

ስለዚህ፡ በየግላችሁ የተሰማችሁንና የሚሰማችሁን፡ ለእናንተው ልተወውና፡ እኔ፡ መቼም፡ የተልእኮ ግዴታ ስላለብኝ፡ የራሴን ዓቅም ሳጠናክርና፥ ፍላጎቴንና ምርጫዬንም ልሠዋና፡ "ለመኾኑ፡ የእነዚያ ኹለት አጽዋማት ምሕላዎች፡ ለእያንዳንዳችን፡ ምን ውጤትን አስገኙ?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱን ለማበርከት፡ በበኩሌ፡ የኾነውን፥ የተሰማኝንና የሚሰማኝንም፡ እንዳለፉት ዓመታት ኹሉ፡ ዛሬም፡ ያንኑ፡ ገላልጬ እንድነግራችሁ ፍቀዱልኝ!

ይህንም ሳደርግ፡ "ለእኔ የኾነው፥ እኔን የተሰማኝና የሚሰማኝም፥ ለእናንተ ከኾነው፥ እናንተን ከተሰማችሁና ከሚሰማችሁም፡ ፈጽሞ የተለየ ይኾናል ብዬ!" በማሰብ አይደለም፤ "በአንዱ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በእርግጥ አንድ ነው!" ብዬ በማመን እንጂ::

የዚህ ምክንያቱ፡ ሌላም አይደለ፤ እያንዳንዳችን፡ ለዚያ ጾም፥ ጸሎትና ምሕላ፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና ቆራጥነት ወስነን ስንነሣ፡ በዚያን ጊዜ፡ በእናንተም ኾነ በእኔ፡ በየግላችን ሰውነት ውስጥ ያደረው፡ ያው አንዱ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለኾነ ብቻ ነው።

አዎን! ያለእርሱ አበጋዝነትና አጋዥነት፡ ያን የመሰለውን ሃይማኖታዊ ምግባር ለማድረግ ማሰብ፥ መወጠንና መወሰን፥ ከዚያም፡ አሳቡን፥ ውጥኑንና ውሳኔውን መጀመር፥ ማካኼድና መፈጸም፡ ከቶ አይቻልምና፡፡ ያም መንፈስ፡ ከእግዚአብሔር አብ ሥርፆ፥ በእግዚአብሔር ወልድ ቤዛነት፡ ፍጥረተ ዓለሙን የሞላው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ይህንም እውነታ፥ ማለትም፡ በእናንተም ኾነ በእኔ ያደረው መንፈስ፡ ያ፡ የእውነት መንፈስ የኾነው መንፈስ ቅዱስ መኾኑን፡ በፈጸምነው ጾምና ባሰማናቸው ጸሎቶቻችን፡ ለየራሳችንና ለፈጣሪያችን፥ ለሌላውም ፍጥረት ኹሉ፡ በይፋ አረጋግጠናል፡፡

እንግዲህ፡ እኔ፡ ራሴ፡ በዚህ መንፈስ ኾኜ፡ ለእኔ ስለኾነው፥ እኔን ስለተሰማኝና ስለሚሰማኝም የምናገረው፡ በዚሁ መንፈስ መኾኑን ካወቃችሁልኝ፡ እናንተ ደግሞ፡ ይህን፡ እኔ የምናገረውን የምትሰሙኝ፡ በዚሁ፡ በአንዱ፡ በቅዱሱ የእውነት መንፈስ ተመልታችሁ መኾኑን፡ ለእኔ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ለየራሳችሁና ለእግዚአብሔር፡ በሃይማኖት ልታረጋግጡት፥ በምግባርም፡ እውን ልታደርጉት ይገባችኋል፤ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል፡ መግባባት የሚኖረው፡ እንዲህ፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ ሲገናኙ ብቻ ነውና፡፡

ይህን የመሰለውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፡ በየፈርጁ ሳቀርብላችሁ፡ አንድ ልዩ፥ ወይም፡ ከባድ፥ ወይም፡ እንግዳ፥ ወይም፡ ድንቅ የኾነ ነገር ያመጣሁላችሁ፥ ወይም፡ ያመጣሁባችሁ፥ ወይም፡ እናንተን፥ ወይም፡ እኔን፡ ከሌሎች ሰብአውያን ፍጡሮች ወገኖች ለይቼ፡ ንጹሓን፥ ፍጹማንና ቅዱሳን ማድረጌ እንዳይመስላችሁ፡ ላስጠነቅቃችሁ እወድዳለሁ፡፡

ይህን፡ አኹን፡ እኔ የምገልጽላችሁን እውነታ፡ ምናልባት፡ ሳናስተውለው ቀርተን ይኾናል እንጂ፥ ወይም፡ ከቁም ነገር ስላልቆጠርነው እንጂ፥ ወይም፡ ንቀነው፥ ወይም፡ ቸል ብለነው፡ ስለተውነው እንጂ፡ በውጪአችንና በአጠገባችን፡ ምንጊዜም፡ አብሮን ያለ፡ የተፈጥሮ ይዞታችን መኾኑን፡ በእርግጥ ልትገነዘቡት የሚገባ ነው።

እንደምንተነፍሰው አየርና እንደምታበራልን ፀሓይ፥ እንደምንረካበት ውኃና እንደምንረማመድባት ምድር ማለት ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ እንዲያውም፡ በውስጣችን ተዋሕዶንና የተፈጠርንበት ባሕርያችን ኾኖ እናገኘዋለን:: እያንዳንዳችን፡ እየራሳችንን፡ በእውነተኛው መንፈስ እንዲገኝ በምናደርግበት፡ በዚህ ጊዜ፡ ይህን ግልጽ ምሥጢር፡ እናንተ ለመረዳት፥ እኔም ለማስረዳት የምንቸገር አንኾንም::

በእነዚያ ኹለት የአጽዋማት ምሕላችን ጊዜያት ቀርቶ፡ በዚች አፍታ፡ ለጥቂት ቅጽበት፡ በጥልቅ ለማስተዋል በመሞከር ብቻ እንኳ፡ ውሳጣዊዉን እየራሳችንን ብንመርምር፡ ከዚህ እውነታ፡ በቀላሉ ልንደርስ እንችላለን:: ይህንም፡ እስኪ፡ እንዲህ እያልሁ፡ ልግለጽላችሁ!

ያ፡ በእውነት መልኩ፡ እርሱን መስለን እንድንፈጠር ፈቃዱ የኾነው እግዚአብሔር አብ፡ ዛሬ ያለው፡ የት ይመስለናል? እንዲህ፡ በመልኩ ከፈጠረን በኋላ፡ በራሳችን ፍላጎትና ምርጫ፡ ወደወደቅንበት የውርደትና የርኵሰት አዘቅት፡ በሰውነት መጥቶ፡ በመሥዋዕትነቱ ያዳነን፡ ያ፡ ራሱ፡ እውነት የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ዛሬ፡ የት የሚገኝ ይመስለናል? በእርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ የእውነት ጸጋ ኾኖ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በምልዓት የወረደው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬ የሚኖረው፡ የት ይመስለናል? <u>**በየራሳችን ውስጥ አይደለምን? በየራሳችን ውስጥ መኾኑንማ፡**</u> ያ፡ የእውነት መንፈስ፡ ያለማቋረጥ እያስገነዘበን እኮ ነው!

አዎን! በውስጣችን ያለው፡ ያ፡ እንድናስብ፥ ያሰብነውንም ኹሉ፡ በንግግርና በሌሎቹ ዘዴዎች እንድንገልጽ፥ ያ፡ ክፉውንና ደጉን፡ ለይተን እንድናውቅ፥ ያ፡ "ሕያው ነኝ እንጂ፡ አልሞትም!" ብለን እንድናምን የሚያደርገን፡ "ነፍስ"፥ ወይም፡ "ኅሊና" የምንለው፡ የተፈጥሮ ባሕርያችን እኮ ነው፡ እግዚአብሔር:: የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የክርስቶስ መንፈስ፥ የእውነቱ መንፈስ የምንለው መንፈስ ቅዱስ፡ አዎን! ኹሉን የሚያሳውቀንና የሚያስተምረን እኮ፡ እርሱ ነው::

ታዲያ! እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ይህን እውነታ ማወቅ፥ ማስተዋልና መረዳት፡ እንደምን አቃተው? እንዴትስ ተሣነው? <u>አዎን! ይህን እውነታ ለማወቅ፥ ለማስተዋልና ለመረዳት ስላልፈለገ ብቻ ነው፡፡</u> ስለዚህ፡ እኔ፡ ስለጾመ ኢትዮጵያና ስለሰላም ለኢትዮጵያ ጾም የምሕላዎች ውጤት የምናገረውን ኹሉ፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ ብቻ ሳትኾኑ፡ ሰብአዊ ፍጡር የኾነው ኹሉ፡ ከፈለገ፡ አበክሮ ሊያውቀው ይቻለዋል ማለት ነው።

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ኅሊና ውስጥ ስላለና ያም ነፍሳዊ ህልውና፡ የዚያ፡ የሰብአዊው ፍጡር፡ የተፈጥሮ ባሕርዩ ስለኾነ፡ እርሱን፡ እግዚአብሔርን፡ ኹሉ ሰው፡ ያውቀዋል፤ በሥጋዊው ሥነ ፍጥረት ገዝፎ የሚሠራውና በሰብአዊው ኅሊና ውስጥ አድሮ፡ በመንፈስ የሚታሰበው፡ ያ፡ "እግዚአብሔር" የምንለው፡ ፈጣሪ አምላክ፡ እርሱ ነውና፡፡ ለዚህ እውቀት ለመብቃት ደግሞ፡ የተለየ ነቢይነት እንደማያስፈልግ፡ በዚሁ ብቻ፡ በቀላሉ ገምተን ልናስተውለው፡ ለማነኛችንም የሚከብደን አይደለም፡፡

እርግጥ፡ በዚህ ረገድ፡ በመካከላችን ልዩነት፥ ወይም፡ መበላለጥ ሊኖር ይችላል፤ ያም ልዩነት፥ ወይም፡ መበላለጥ፡ ሌላው፡ ይህን እውቀት ባለመፈለግ፡ በራሱ ምርጫና ውሳኔ፡ በውስጡ ተዳፍኖ እንዲቀር ሲተወው፥ እኛ ግን፡ ከፈጣሪያችን፡ በተፈጥሮ በተለገሠን፡ የመምረጥ ነጻነታችንና የመወሰን ሥልጣናችን ተጠቅመን፡ በውስጣችን ከተዳፈነበት፡ ገላልጠን እንዲከሠት ለማድረግ መቻላችን ብቻ ነው፡ ልዩነቱ፥ ወይም፡ መበላለጡ፡፡

ይህን ክሥተት፡ እያንዳንዳችን የጾሙ ተሳታፊዎች፡ ከጾመ ኢትዮጵያና ከሰላም ለኢትዮጵያ ጾም፡ የሃይማኖታዊ ምግባር ተክሎቻችን ላይ ከለቀምናቸው፡ የንስሓና የእውቀት ፍሬዎች፡ አንደኛው ኾኖ እንድንጠቀምበትና እንድንሞገስበት፡ ይኸው ተበርክቶልናል፡፡ እንዲህ ከኾነ፡ ይኸው እውቀት፡ በእናንተም፥ በእኔም ውስጥ ስላለ፡ በዚህ ረገድ ያለው፡ የኹለታችንም ወገኖች አሳብ፡ አንድ መኾኑን እንመሰክራለን።

ይህም፡ "ለእኔ የኾነው፥ እኔን የተሰማኝና የሚሰማኝም፥ ለእናንተ ከኾነው፥ እናንተን ከተሰማችሁና ከሚሰማችሁም፡ ፈጽሞ የተለየ አይደለም!" በማለት፡ ከላይ የገለጽሁትን እምነቴን ያጠናክረዋል፡፡

ታዲያ! ስለዚሁ፡ የጋራችን ስለኾነው እውቀት፡ በተለይ፡ እኔ እንድናገር ያስፈለገበት ምክንያት፡ ከቶ ምንድር ነው? ወይስ፡ ለዚህ ተልእኮ፡ እኔን፡ በተለይ የሚያገባኝ የኾነበት፡ ምን አስገዳጅ ነገር አለ?

ይህን፡ የራሴን ጥያቄ መሠረት በማድረግ፡ ምናልባት፡ እያንዳንዳችሁም፡ “እርሱ፡ ከሌሎቻችን ተለይቶ፡ ይህን ጥሪና መልእክት ያስተላለፈው፡ ማን ኾኖ ነው? ምንስ ኃላፊነት ኖሮበት ነው?” የሚሉ አስተሳሰቦች፡ በየአእምሮአችሁ ውስጥ ሊነሣሡ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡

እነዚህ ጥያቄዎቻችሁ፡ ትክክለኛና ተገቢ ስለኾኑ፡ ለእነርሱ፡ ባጭሩም ቢኾን፡ እንዲህ የሚለውን መልስ እሰጣለሁ፡- አዎን! እንደማነኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ኹሉ፡ እኔንም፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ የሚያስጠይቀኝ፡ ቀዳሚ ኃላፊነት አለኝ፤ ከዚህ ሌላ፡ በግል የተጣለብኝ፡ ተጨማሪ ግዳጅ ደግሞ አለብኝ፡፡ ይህንም፡ ለምታውቁኝ ሳይኾን፡ ለማታውቁኝ፡ እንደሚከተለው፡ በማጠቃለል ልግለጽላችሁ!

በቅዱሱ ኪዳን ጸንቶ የኖረው፡ የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ ከሰዎች ስለመወገዱ፡ "ደርግ" የተባለው፡ ሰይጣናዊ የቅጣት አገዛዝ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. በይፋ ማስታወቁ ይታወሳል፤ ይህም የኾነው፡ ራሱን፡ ለቅዱሱ ኪዳን አፍራሽነት ፍዳ በዳረገው፡ በዚህ፡ በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የሃይማኖት ክህደት፥ ዓመፅና አመንዝራነት ምክንያት መኾኑ፡ ተደጋግሞ ተነግሩዋል፡፡ እስከዚያን ዘመን ድረስ፡ እኔ፡ በዚያ፡ በእግዚአብሔራዊው ሥርዓተ መንግሥት ሥር ባሉት፡ በሦስቱም የአገልግሎት ዘርፎች፡ ማለትም፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ፡ በተለያዩ ኃላፊነቶች ተመድቤ፡ ተልእኮዬን (አገልግሎቴን)፡ ፈጽሜአለሁ፡፡

ይኸውም፡ የመጨረሻዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡ የቤተ ሕዝቡ የሕግ መምሪያና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶች አባል፥ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያኄና የቤተ ምልክናው፡ የአኵስም ጽዮንና የአውራጃዋ አስተዳዳሪ በመኾን የሰጠሁትን አገልግሎት የሚያካትተው ግዳጅ ነው፡፡

ይህንኑ ግዳጄን፡ በኹለት ዐረፍተ ነገሮች አሳጥሬ ሳቀርበው፡ ከዚህ በሚከተለው መልክ ተጠቃልሎ ይገኛል፡-

፩ኛው፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ በኪዳናዊነቱ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን፡ የሦስቱንም ቤቶች ጸጋዎች፡ ማለትም፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን የማገልገል ግዳጅ፡ እንደማነኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የተቀበልሁ መኾኔ ነው፤

፪ኛው፡ ከላይ የተጠቀሱትን የግዳጅ ሥልጣናት፥ በይበልጥም፡ እነዚህን ሦስት ቅርንጫፍ የአገልግሎት ዘርፎች ያዋሐደውን፡ የንቡረ እድነቱን ሥልጣን፡ ከሕጋዊው የዘመኑ መንግሥት ተቀብዬ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ ከእያንዳንዱ የኪዳኑ ተዋዋይ የሚጠብቀውን ታማኝነት፡ ዓቅም በፈቀደ፡ ያላጓደለውን አገልግሎቴን፡ ከአምሣ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ በእሥራቱና በግዞቱ፥ በስደቱም ጊዜ ሳይቋረጥ፡ የቀጠልሁ መኾኔ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ከእግዚአብሔር በወረስነው ሥርዓተ መንግሥታችን መሠረት፡ የእግዚአብሔር የኾነችውን፡ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያ መልእክት ለማድረስ የሚያበቃው፡ አስፈላጊውና ተገቢው የተልእኮ ግዳጅ እንዳለብኝ ለመረዳት፡ ለማንም ግልጽ ይመስለኛል።

ለተያያዝነው ቍም ነገር፡ መነሻና መንደርደሪያ ይኾነን ዘንድ፡ ይህን ያህል ከገለጽሁላችሁ፡ ወደፍሬ ጒዳዩ ዘልቄ ልግባና፡ በልቦናዬ ያለውን ልንገራችሁ! እንግዴህ፡ በጾመ ኢትዮጵያና በሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ማብቂያዎች ላይ፡ በበኩሌ፡ በኅሊናዬ መድረክ ላይ፡ በመንፈስ ያገኘሁትን መልስ፡ ምንም ሳላስቀርባችሁ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም አካፍላችኋለሁና፡ ስሙኝ!

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታዊና ምግባራዊ አቋሜ፡ ቀድሞውኑ፡ በጾመ ኢትዮጵያ መልእክት ውስጥ የተጠቃለሉትን እውነታዎች መሠረት አድርጎ የቆየ በመኾኑ፡ ለሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ጭምር፡ የተሰጠውን መመሪያና የተሠራውን ሥርዓት፡ በተግባር ላይ አውዬ ለመፈጸም አልተቸገርሁም።

ስለዚህ፦ ፩ኛ፡ <u>በራሴ በኩል፡</u> ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን የተነሣ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችውና የትንሣኤ ሕይወት በሰፈነባት፡ በፍጥረተ ዓለሟ ኢትዮጵያ ውስጥ የመኖሬ ጸጋ፡ የቀጠለ ኾኖ አገኘሁት።

፪ኛ፡ <u>በእግዚአብሔር በኩል፡</u> ከባሕርዩ ከፍሎ፡ በመልኩ ለፈጠራት ነፍሴ፡ በመለኮታዊ ጥበቡ፡ የእናቴ የማሕፀን ደምና የአባቴ የአብራክ ዘር ተዋሕደው፡ እንዲያስገኙት ያደረገውን፡ የሥጋ አካል ከማልበሱ ጀምሮ፡ በቅዱስ መንፈሱ ወልዶኝ፡ መንፈሳዊዉን አካል እስከመጎናጸፍና በትንሣኤ ሕይወት ለመኖር እስከመብቃት የደረስሁበትን፡ የህልውና ዘውድ እንዳቀዳጀኝ፡ በበለጠ አወቅሁ።

ለዚህ ምድራዊ ኑሮዬም፡ አገሬን ብቻ ሳይኾን፡ መላውን ፍጥረተ ዓለም እንድጠቀምበት እንዳዘጋጀልኝ፥ ተጻራሪዎቼን፡ ክፉውን የሰይጣን ኃይል፥ ኃጢአትንና ሞትንም፡ ለመቼውም ጊዜ፡ በቤዛነቱ አስወግዶ፡ ወደቀደመችው የገነት ህልውና፡ በንስሓዬ ፍሬና በሥጋ ወደሙ ማኅተም እንደመለሰኝም፡ አበክሬ ተገነዘብሁ።

እውነተኛና ፈቃደኛ በኾነ፡ በማነኛውም ሰብአዊ ፍጡር ልቦና ውስጥ፡ በፍጹም ነጻነትና ፍቅር እንድትሰፍን የደነገገበትን፡ ዘለዓለማዊት የሰላም መንግሥቱንም እንዳወረሰኝ፡ በተመስጦ ተሰማኝ።

ዛሬም፡ በዚህ ሥጋዊ ሕይወቴ፡ ከሕፃንነቴ አንሥቶ ከደረሰብኝና ከሚደርስብኝ ፈተናና መከራ፥ እሥራትና ስደት፡ በአደራ ከሰጠኝ ቤተሰቤ ጋር እንደጠበቀኝና እንደሚጠብቀኝ፡ በበለጠ አረጋገጥሁ።

በዚህ ኹሉ፡ እጅግ ተደስቼ፡ ለዚህ ቸርነቱና ምሕረቱ፥ ፍቅሩና ጸጋው፥ በአጠቃላይ፡ ኢትዮጵያን የመሰለች አገር፥ ኢትዮጵያዊነትንም የመሰለ ሃይማኖት፡ በቃል ኪዳን ስለለገሠን፡ ወሰን የሌለውንና ሊገለጽ የማይቻለውን ምስጋናዬን፡ ለፈጣሪያችንና አምላካችን፥ መምህራችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ሊቀ ካህናታችን፥ ንጉሣችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እንዲሁም፡ ለሃይማኖታችንና አገራችን፥ ንግሥታችንና እናታችን ድንግል ማርያም አቀረብሁ።

፫ኛ፡ በሰው በኩል ያለው፡ ነገር፡ ከላይ ከገለጽኋቸው ከኹለቱ መልካካም ኹኔታዎች፡ የተለየና የክፉው ወገን ኾኖ ስለሚገኝ፡ ስለእርሱ መቀጠሉ ይጨንቀኛል፤ ይከብደኛልም፡፡ ይኹን እንጂ፡ የተልእኮ ግዳጄ ነውና፡ ጭንቀቴንና ክብደቱን አስወግጄ፡ እናገረዋለሁ።

የምናገረውም፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል፡ በመሓላ ከተደረገው፡ "ቅዱሱ ኪዳን" ከምንለው፡ የቃል ኪዳን ስምምነት የተነሣ፡ መልካም ጎን ስላለው ነው፤ በዚህ ስምምነት፡ ከሰው በኩል የተገኘው ውጤት፡ የክህደት፥ የዐመፅና የምንዝርና መራራ ፍሬ ሲኾን፡ በእግዚአብሔር በኩል ግን፡ የታማኝነቱ፥ የትዕግሥቱና የምሕረቱ አምላካዊ ቸርነት ጸንቶ የቀጠለ በመኾኑ፡ መዳናችን፡ አኹንም፡ በግልና በአገር ብቻ ሳይኾን፡ በዓለም አቀፉም ደረጃ በመረጋገጡ፡ ይህን ለማለት አስችሏል።

ይህን እውነታ፡ በእውነት አምነውበት፡ ለሚያመልኩት ታማኞች ተከታዮቹ፡ በቅዱስ መንፈሱ የሚገለጠው፥ ያ፡ በኅሊናዬ ያለው እግዚአብሔር፡ በጾመ ኢትዮጵያና በሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ፍጻሜዎች ላይ፡ ለእኔም፡ እንደማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ገልጾልኝ እንዳስተውለው አደረገኝ፡፡

አዎን! መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እንደሚያደርገውና በቀደሙት ዓመታት፡ በጾመ ኢትዮጵያና በሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ጊዜያት እንደፈጸምናቸው ቀኖናት ኹሉ፡ ባለፈው፡ በ፳፻፪ቱ ዓመተ ምሕረት፡ የሦስቷና የአምስቷ ቀናት ጾምና ጸሎት፥ ምሕላና ስግደት፡ የቀረበለትን፡ የእኔንም አቤቱታ ሰምቶ ኖሮ፡ በኅሊናዬ ውስጥ ያሳደረውን ነፍሳዊ የእውቀት ባሕርይ፡ በፍጻሜው ላይ፡ በቅዱስ መንፈሱ ቀሰቀሰው!

ቀስቅሶም፡ በንስሓ ለመመለስ ፈቃደኛ ኾኖ ስላልተገኘው፡ ስለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ "ምን አድርግ ነው፡ የምትለኝ?" በሚለው የኃዘኔታ ጥያቄው፡ ለአቤቱታዬ መልስ ሰጠኝ፡፡

እኔም፡ ከፊቱ ወድቄ፡ "ጌታዬ! አምላኬ! አቤቱ! እንግዴህ፡ እባክህ ይብቃ!" አልሁት፡፡

እርሱም፡ "ምኑ?" አለኝ።

ኹሉን የሚያውቅ ፈጣሪ በመኾኑ፡ ለዚህ፡ መለኮታዊ ጥያቄ፡ መልስ መስጠት እንደማያስፈልገኝ ተገንዝቤ፡ ጸሎቴን፡ እንዲህ እያልሁ ቀጠልሁ፡-

"በቅድስት እናትህ ስም የሚጠራውንና ለእርሷ፡ 'ልጆቿ' አድርገህ የሰጠኸውን፡ ይህን የኢትዮጵያ ትውልድ፥ ደግሞም፡ በእርሷ ስም የምትጠራውንና ለእርሷ ርስት ጕልት አድርገህ የሰጠሃትን፡ ይህችን የኢትዮጵያን ምድር፡ የትውልዱን፡ የሃይማኖት መጓደልና የምግባር መሰነካከል ሳትመለከት፡ እንዲያው፡ ስለቅዱሱ ስምህ ስትል፥ በእናትህ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረትነት፡ በአንተና በእኛ መካከል ጸንቶ ስላለው፡ ስለቅዱሱ ኪዳንህም ስትል፥ እንዲሁም፡ ስለባለሟሎችህ መላእክት፥ በሕይወተ ሥጋና በሕይወተ ነፍስ ስላሉት፡ ታማኞች አገልጋዮችህ ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታትም ስትል፡ በቀደሙት ዘመናት ስታደርግ የኖርኸውን፥ እኔም፡ ይኸው፡ በሕይወተ ሥጋ ቆሜ፡ በዓይኔ እንዳይ ያደረግኸኝን፡ ይህን የቸርነት ሥራህን አስታውሰህ፡ ዛሬም ደግሞ፡ እባክህ ይቅር በል!"

ስሟን ስለጠራሁ፡ ታማኞች አገልጋዮቿ፡ "አፍጣኒተ ረድኤት!" (ፈጥና ለእርዳታ የምትደርስ) የምንላት እመቤታችን፡ ድንግል ማርያም፡ በዚያው ኅሊናዬ ውስጥ ስላለች፡ ድንገት፡ በልቦናዬ መድረክ ላይ በመንፈስ ተገልጣ፡ "**ልጄን፥ ወዳጄን ምን አድርግ ነው የምትለው?**" ስትል እንደጠየቀችኝ ተሰማኝ።

እኔም፡ በዚህ ድንገተኛ ኹኔታ፡ ለጥቂት ተደናግጬና መንፈሴ ታውኮብኝ፡ ከወደቅሁበት ሳልነሣ፡ እንደተደፋሁ፡ "ውይ!? እምዬ፥ እመቤቴ! ቅድስት ድንግል! አንቺም!?" አልኋት።

እርሷም፡ በጽኑ ቃል፡ "**አዎን! ልጆቼን፥ ይኼን የዛሬውን ትውልዴን የምፋረድ፡ እኔ ነኝ እንጂ፡ እርሱ፡ ልጄ፥ ወዳጄ አይደለም!**" አለችኝ፤

ቃሏንም፡ እንዲህ ስትል ቀጠለች፡- "እርሱማ፡ 'ድል አድራጊው አንበሳ'፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ዓመት፡ በራሱ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ፈጽሞ ይቅር ብሎ፡ ለመቼውም ጊዜ፡ ምሕረቱን አድርጓል። ምን ቀረበትና ነው፡ አኹን፡ እንደገና 'ይቅር በል!' የሚባለው?

"ልጄ፡ ወዳጄ፡ ይህንኑ ምሕረቱን፡ በእኔ ዋስትና፡ በቃል ኪዳኑ ዐትሞ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ሰጥቷል፤ ለዚህ ይቅርታውና ምሕረቱ፡ ማረጋገጫ የኾነውን፡ ሥጋውንና ደሙን፡ በእንጨት ላይ ራቁቱን ተሰቅሎና በጦር ተወግቶ ሲቆርስ፥ ሲያፈስስም፡ እኔ እናቱ፡ ከመስቀሉ አጠገብ ቆሜ፡ በዓይኖቼ ተመልክቻለሁ፤ ይህንኑ የተቆረሰ ሥጋውንና የፈሰሰ ደሙን፡ ከመስቀል ባወረዱት ጊዜ፡ አቅፌው፡ በሰውነቱ ላይ እንዳለ፡ በእጆቼ ዳስሼና አብሼ፡ ስሜዋለሁ፡፡

"የይቅርታውና የምሕረቱ ማረጋገጫ የኾነው፡ ይኸው ሥጋውና ደሙ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ያለማቋረጥ፡ በየቀኑ፡ በየቤተ ክርስቲያኑ፡ እንዲዘጋጅ እያደረገም፡ እነሆ፡ 'ብሉኝ! ጠጡኝ!' በሚለው በጸሎተ ቅዳሴው ያውጃል፤ በቅዱስ ቁርባኑም ግብዣ፡ በሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስም፡ ለተራበውና ለተጠማው፥ ለታረዘውና ለታመመው፥ ለታሠረውና ለተሰደደው ኹሉ፡ ያለከልካይና ያለዋጋ፡ በፍቅርና በሰላም፥ በነጻነትና በሐሤት ያቀርበዋል፡፡

“ታዲያ! ከእርሱ፡ ከልጄ፥ ከወዳጄማ፡ ምን የጎደለበት፥ የቀረበትም ነገር ኖሮ ነው፡ አኹን፡ እንደአዲስ፡ ይቅርታና ምሕረት የሚጠየቀው? ይህንም፡ አንተም ታውቀዋለህ፡፡” አለችኝ፡ በዚያው በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፡፡

እኔም፡ ዓይኖቼን ጨፍኜ እንደተደፋሁ፡ “አዎን! እናታችን! ቅድስት ድንግል! አውቀዋለሁ፡፡” በማለት ፈጥኜ፡ በጎሊናዬ መለስሁላት፡፡

“ታዲያ ካወቅኸው፡ ለምን፡ ልጄንም፥ እኔንም፡ ታስቸግረናለህ?” ያለችኝ መሰለኝ፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፥ መደንገጤንና መፍራቴን አውቃ፥ መለስ ባለ የለሰለሰ ድምፅ፡፡

“ቢቸግረኝ ነዋ! እምዬ! እመቤቴ! ታዲያ ምን ላድርግ? ወዴትስ እኼዳለሁ?” ብዬ፡ በዚያው፡ በጀመርሁት የፍቅር ድፍረቴ መለስሁላት፤ ንግግሬንም በመቀጠል፡ “ለልጅሽና ለአንቺ፡ 'አቤት!' ከማለት በቀር፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ሌላ የምንጮህበት፡ ምን መኼጃ አለን? ይህንማ፡ አንቺ ያስተማርሽን ሥርዓታችን አይደለምን?” አልኋት፡ አኹንም፡ በዚያው፡ በጎሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፡፡

እርሷም፡ "በዚህ ሃይማኖትህና ምግባርህ በመጽናትህማ፡ ይኸው፡ ለዚህ ዕድል በቅተሃል! አኹንም፡ የእኔ ብቻ ሳይኾን፡ የፈጣሪዬም ልጅ የኾነው፡ ይህ፡ በስሜ የተጠራው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፥ ርስት ጕልት ኾና የተሰጠችኝ፡ ይህችም ምድር፡ ከልጄና ከእኔ ስም፥ ከቅዱሱ ኪዳንና በዚሁ ኪዳን ጸንተው ከሚገኙት ታማኞች ልጆቼ ገድል የተነሣ፡ ኹለቱም አይጠፉም!" የሚል፡ የሚያጽናና ቃልን አሰማችኝ፡፡

በዚህ ቃሏ፡ መንፈሴ፡ በበለጠ ተነቃቅቶና ዕዝነ ልቦናዬ ለመስማት፡ ወደቃሏ አዘንብሎ ሳለ፡ በዚያው፡ በኀሊናዬ ውስጥ እያለሁ፡ ምሥራቿን፡ እንዲህ ስትል፡ ቀጠለችልኝ፡- "ለዚህ ሕዝቤ፡ ለእያንዳንዱ ግለሰብ ሳይቀር፥ ለዚች ምድሬም፡ የበጃቸውና የጠቀማቸው፡ ቅዱሱ ኪዳንና የእርሱ፡ የቅዱሱ ኪዳን መኖር ነው፡፡ እርሱንም፡ የቀደሙት፡ ታማኞቹ አገልጋዮቼ፡ የዚህ ሕዝቤ አባቶቹና እናቶቹ፡ ከጥንት ጀምረው የነበሩት፥ ዛሬም ያሉት፥ አንተ፡ በአካለ ሥጋ የማታውቃቸው፥ ልጄና እኔ ግን የምናውቃቸው፡ ጥቂቶቹ ጭምር፡ አክብረውና ጠብቀው፥ በመሥዋዕትነታቸውም፡ አጽንተውት፡ እስከዚህ ጊዜ አቆይተውታል፡፡

"ይህን እውነታ፡ ወገኖችህና ሌላው ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ እንዲገነዘቡት ለማድረግ፡ መንፈስ ቅዱስ ባመለከተህ፡ የምታካኺደውን ጥረት አታቋርጥ! ይህን ጥረትህን፡ በመፃረር፡ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ፡ በግልጽም፥ በሥውርም፡ እየገጠመህ ያለውን ብርቱ ተቃውሞ፡ ልጄና እኔ እናያለን፤ ይህ አገልግሎትህ፡ የተጠራህበት ተልእኮህ ብቻ ሳይኾን፡ ገድልህም ስለኾነ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር ነውና፡ በሚደርስብህ ጥቃት ሳትዳከም፡ ቀጥልበት!" አለችኝ፡ እመቤቴ፡ በሚያጽናና ቃሏ።

ከዚህ የተከተለውን ንግግርዋን የጀመረችው፡ "ግን፡" በሚለው ቃል ስለኾነ፡ "እመቤቴ፥ አኹን ደግሞ፡ ምን ልትለኝ ይኾን!?" ብዬ፡ መንፈሴ፡ በድንጋጤ፡ እንደገና ሊታወክብኝ ሲቃጣው፡ "ግን፡ ለልጆቼ የምታደርስላቸው መልእክት ይህ ነው፡-" የሚለውን ቃሏን፡ በእዝነ ኅሊናዬ ስሰማው፡ ተረጋጋሁና፡ ከተደፋሁበት፡ ቀና አልሁ፡ በፊቴ ያለች መስሎኝ፡፡

ለካ ንግግራችን የሚካኼደው፡ በመንፈስ ኖሮ፥ በአካለ ሥጋ ላያት የምችል መስሎኝ፡ ቀና በማለት፡ በፈጸምሁት የስሕተት አድራጎቴ፡ እጅግ ተጸጸትሁ፤ ይህ አድራጎቴ፡ “ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ ብፁዓን ናቸው!” ከሚለው፡ ከኢትዮጵያውያን ብቸኛ ባለቤትነት፡ ውጪ የሚያደርገኝ ታላቅ ጥፋት መኾኑን አምኜ፡ ፈጣሪዬን፡ በቅጽበት ንስሓዬ፡ “ይቅር በለኝ!” ብዬ ከለመንሁት በኋላ፡ ያለሁበትን እውነታ በመቀበል፡ ወደነበርሁበት ስግደቴ፡ እንደገና ተመልሼ፡ በግንባሬ ተደፋሁ፡፡

እመቤቴ፡ ድንግል ማርያምም፡ “ለልጆቼ የምታደርስላቸው መልእክት፡ ይህ ነው፤” ስትል፡ መናገርዋን፡ እንዲህ በሚል ቃል ቀጠለች፡-

“'የጎደለው፥ የቀረው፡ ከልጄ፥ ከወዳጄ ሳይኾን፥ ከእኔም፡ ከእናታችሁ ሳይኾን፡ ከእናንተ ነው፤ ቅዱሱን፡ የይቅርታና የምሕረት ኪዳን፡ በሃይማኖታችሁ ጉድለትና በምግባራችሁ ርኵሰት ልታፈርሱ የሞከራችሁ፡ እናንተ ናችሁ፤ ኪዳኑ፡ መለኮታዊ ስለኾነ፡ በዘለዓለማዊነቱ፡ በየጊዜው እየጸና የሚኼድ ከመኾኑ በቀር፡ በማንም ፍጡር ሊፈርስ ቀርቶ፡ ሊነካ አይቻልም፤ ሊያፈርሰው የሚሞክር ቢኖር፡ ያ የሞከረው ፍጡር፡ ራሱ ይፈርሳል እንጂ፡ እርሱ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ አይነካም፡፡

“'ልጄ፡ ቅዱሱን ኪዳን የሰጣችሁ፡ እናንተን ለመጥቀም፥ ለእናንተው ደኅንነትና መልካም ሕይወት እንዲኾንላችሁ እንጂ፡ ለሰጪው፥ ለእርሱ፥ ለእግዚአብሔር የሚያስፈልገው ኾኖ አይደለምና፡ ለየራሳችሁ ጥቅም ስትሉ፡ ኪዳናችሁን ጠብቁት!

"ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በከፈለው መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ እኔ እናቱ፡ ሕያው ማደሪያውና ዋስትናው፥ ምስክሩና ምልክቱ የኾንሁለት፡ ይህ ቅዱሱ የምሕረት ኪዳን፡ ከእናንተ፡ ከእያንዳንዳችሁ የሚጠይቀውን፡ የየበኩላችሁን ግዳጅ ፈጽሙ! የአኹኑ ግዳጃችሁ፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአመንዝራነት ኃጢአታችሁ ምክንያት፡ በየራሳችሁ ላይ የወረደውን ፍዳ፡ <u>በእውነተኛ ንስሓ ማስወገድ ነው።</u>

ይህን ካላደረጋችሁ፡ የልጄን ይቅርታውንና ምሕረቱን አታገኙትም። በዚያው ኃጢአታችሁ እስካላችሁ ድረስ፡ እንዴት ልታገኙት ይቻላችኋል? አይቻላችሁም። የእያንዳንዳችሁን ጥፋትና የኀብረት በደላችሁንማ፡ እናንተ ከምታውቁት በላይ፡ ልጄም፥ እኔም እናውቀውለን፤ ከእኛ ልትሸሽጉት አይቻላችሁም:: ቅዱሱን ኪዳን፡ አክብራችሁ ስትጠብቁት፡ በክብር ይጠብቃችኋል፤ ንቃችሁ ስትተዉት ግን፡ ለየራሳችሁ የሰውነት ፈቃድና ፍላጎት፡ አሳልፎ ይሰጣችኋል፤ ለፍጹም ድምሳሴ ግን፡ አይዳርጋችሁም፤ በንስሓ ስትመለሱ፡ በሐሤት ሊቀበላችሁ፡ ይጠባበቃችኋል:: ስለዚህ፡ ተመለሱ!

"'የእግዚአብሔር መንግሥት የምትሰፍነው፡ በሰዎች ልቦና ውስጥ እንደኾነ ታውቃላችሁ፤ እንዲህ ከኾነ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በየልቦናችሁ ውስጥ ትሰፍን ዘንድ፡ ሰውነታችሁ፡ በእርግጥ፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውን?

"በልጄ ላይ ያላችሁ፡ የሃይማኖትና የአምልኮት ታማኝነታችሁ፡ እንዴት ነው? እስከምንስ ነው? በምግባራችሁስ፡ እንዴት ናችሁ?

"ለመኾኑ፡ ዛሬ የምትኖሩት፡ ልጄ፡ በጥንቱ፥ በመካከሉና በመጨረሻው ዘመናት፡ የሠራላችሁን ሥርዓት ተከትላችሁ ነውን? በኹለንተናችሁ ሠልጥኖ፡ በነጻነት እንዲመራችሁ የተቀበላችሁት፡ ማንን ነው? የእርሱን ቅዱስ መንፈስ ነውን? ወይስ፡ በባርነት እንዲገዛችሁ የፈቀዳችሁለት፡ ባዕዱ፡ ክፉው መንፈስ ነው?

"እስኪ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነት መርምሩ! ኹለንተናችሁ፡ በሃይማኖታችሁና በአምልኮታችሁ፥ በምግባራችሁና በኑሮአችሁ፡ ፍጹም ንጹሕ ነውን? ልጄ፥ ጌታዬና አምላኬ፡ የሚቀበለው አምልኮ፡ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብለትን ብቻ መኾኑን ታውቃላችሁ፤ እንዲያ ከኾነ፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ፡ ለእርሱ እውነተኛ አምልኮና ሕይወት ስለማብቃታችሁ፡ በሰው ፊት ቀርቶ፡ በየኅሊናችሁና በእግዚአብሔር ፊት ትመሰክራላችሁን?

"'ስለእኔስ ያላችሁ ፍቅር፡ ከልባችሁ፡ የእውነት ነውን? ወይስ በአንደበት ብቻ የሚነገር ነው? እንደልጄ የአደራ ቃል፡ እኔ፡ እናታችሁ፥ እናንተም፡ ልጆቼ ከኾናችሁና በስሜ ከተጠራችሁ፡ የምትኖሩት፡ ቃሌን ሰምታችሁና ተቀብላችሁ፡ ልጄ በሠራላችሁ ሥርዓት ነውን?

አለዚያ፡ እንዴት 'ልጆቼ!' ተብላችሁ፡ በልጄ ስም፡ 'ክርስቲያኖች'፥ በእኔም ስም፡ 'ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት' ተብላችሁ ልትጠሩ ትችላላችሁ? አይኾንም፤ ልጆቼ!

"'በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ፡ የተደረገውን ተአምር ታስታውሱ የለምን? ያ ተአምር፡ እውን የኾነው እኮ፡ በዚያ የነበሩት አገልጋዮች፡ እኔ፡ 'አድርጉ!' ያልኋቸውን ቃሌን ተከትለው ስለፈጸሙት እንደነበረ ታውቃላችሁ። እነርሱ፡ ለዚያ ቃሌ ታዛዦች በመኾናቸው፡ ልጄ፥ ወዳጄ፡ 'ጊዜዬ፡ ገና አልደረሰምና፡ አላደርገውም!' ያለውን ቃሉን ሳይቀር፡ ለእኔ፡ ለእናቱ ሲል አሻሽሎ፡ የምሕረትና የቸርነት ሥራውን ፈጽሞልኝ፡ አስደስቶኛል።

"እናንተ፡ ከልጄ ተለይታችሁ፡ እርሱን የሚያሳዝነውን ጥፋት ልታደርጉ ይገባችኋልን? ልጆቼ ከኾናችሁ፡ እርሱ፡ ፈቃዴን ተቀብሎ እንደፈጸመልኝ፥ እነዚያ አገልጋዮችም፡ ትእዛዜን ሰምተው እንደፈጸሙት፡ እናንተስ፡ ቃሌን ሰምታችሁ፡ የማትቀበሉትና የማትፈጽሙት፡ ለምንድር ነው? (ዮሐ. ፪፥ ፩-፲፩።)

"'በእናንተ፡ በቃል ኪዳን ልጆቻችን በኩል፡ ልታደርጉት የሚገባችሁን፡ ልንገራችሁ ብዬ ነው እንጂ፡ ልጄ እና እኔማ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ እርሱ፡ የአባትነቱን ቸርነት፥ እኔም፡ የእናትነት ርኅራኄዬን አናጓድልባችሁም!' በላቸው።

"እንግዴህ፡ በአንተም አንደበት፡ 'ተዉ! አይኾንም፤ ይበቃል፤ በንስሓ ተመለሱ!' ሊባሉ የሚገባቸው፡ የቃል ኪዳን ልጆቼ፡ እነርሱ እንጂ፡ ልጄ፥ ወዳጄ፡ የቀረበት፡ የቸርነት ሥራ ኖሮ፡ "ይህን አድርግ!' ተብሎ አይጠየቅም፤ ሊለመንም አይገባም!" ስል፡ ቀደም ብዬ የተናገርሁህ፥ ልጄም፡ 'ምን አድርግ ነው፡ የምትለኝ?' ያለህ፥ እኔም፡ አስከትዬ፡ 'ልጄን፥ ወዳጄን ምን አድርግ ነው የምትለው?' ያልሁህ፡ ለዚህ ነው።

“አኹንም፡ ይህን ቃሌን መሠረት አድርገህ፡ ልጄ ያለህን÷ እኔም ያልሁህን፡ ይህን መልእክት፡ ለዚህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ አድርስላቸው!” አለችኝ፡ በዚያው፡ በነበርሁበት፡ የኀሊና ተመስጦዬ ውስጥ እንዳለሁ፡፡

እኔም፡ “እመቤቴ! በዚህ ረገድ፡ በእኔ በኩል፡ የምችለውን ኹሉ፡ በዓቅሜ አድርጌአለሁ፤ ሳልፈጽመው የቀረብኝ ተልእኮ ያለ አይመስለኝም፡፡ ይህንኑም፡ አንቺም÷ ልጅሽም የምታውቁት ስለኾነ፡ ለመግለጽ መሞከሩ፡ የሚገባኝ አይደለም።

የልጅሽንና የአንቺን መልእክት፡ ለትውልዱ ማቅረብ የጀመርሁት እኮ፡ ገና፡ በልጅነት ዕድሜዬ፡ በትምህርት ቤት ሣለሁ ነበር፤ ኋላም፡ ትልቅ ኾኜ፡ በሥራው ዓለም÷ ቀጥሎም፡ በደርግ እሥር ቤት÷ ግዞትና የስደት ኑሮዬ ጊዜያት እንኳ ሳይቀር፡ የተጠመድሁበትን፡ ይህንኑ ተልእኮ በመቀጠል፡ በቃሌና በአካል ተዘዋውሬ በመገኘት÷ በጽሑፍና በመጽሓፍ÷ በዘመኑ የድምፅ መገናኛ አውታሮች ጭምር፡ የአንቺንም÷ የልጅሽንም መልእክት አዳርሼ ጨርሻአለሁ፡፡ በእነዚያ ጊዜያት፡ የተናገርኋቸው ኃይለ ቃላት÷ የጻፍኋቸው ቍም ነገሮችስ፡ ከራሴ የፈለቁ፡ የእኔ ናቸውን? ከማን አገኘሁት÷ ወይስ፡ ከማን ተማርሁት ልል ነው?

"ገና፡ በልጅነቴ፡ ተማሪ ሣለሁ፡ 'ሕፃኑ ሰማዕት፡ ቅዱስ ቂርቆስ!' እና 'እየው ያን መከራ! የደስታ ጮራ!' በሚሉ አርእስት፡ የጻፍኋቸውን ተውኔቶች፡ በሰበካዬ ማርገጃና ድንኳን÷ በትምህርት ቤትና በሕዝብ አዳራሾች መድረክ ላይ ቀርበው እንዲታዩ ያደረገ÷ ከዚያም፡ 'ምናሴ! የመከራዬ ደስታ! ዓለምን ረታ!" የሚለውን መጽሓፈ ራእይ፡ ያስደረሰ÷ ያሳተመና ያሠራጨ÷ በመጨረሻም፡ እውን ያደረገ ማን ነው? በእነዚያ ድርሰቶች አማካይነት የተላለፈው መልእክትስ፡ የማን ኖርዋል?

"በእነዚህ ኹሉ ሥራዎች አማካይነት፡ የተከሠቱት ምሥጢራትና የተላለፉት መልእክታት፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ መንፈስ ቅዱስ የገለጸልኝና ያስተማረኝ፡ የልጅሽና የአንቺው አይደሉምን?

“'ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!' የሚለው መጽሐፍ የተዘጋጀው፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ!' የሚለው ሰው ኹሉ፡ ያን ተመልክቶ፡ የአንቺንና የልጅሽን ማንነት ፈልጎ በማግኘት፡ ከአንቺና ከልጅሽ ለመድረስ፥ በዚህም የፍለጋ ግኝቱ ምክንያት፡ የራሱን ማንነት፡ በትክክል ለማወቅ እንዲችል ለመርዳት አይደለምን? 'ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!' የሚለውስ መጽሓፍ፡ የያዘው ቍም ነገር፡ አንቺ፡ ከልጅሽ በተሰጠሽ ሥልጣን፡ ይኸው፡ እንደዚህ፡ እንደዛሬው ቃልሽ፡ ልጆችሽንና ሰውን ኹሉ፥ ፍጥረተ ዓለሙንም በመላ፡ በልጅሽ ፊት የምትፋረጅበት አይደለምን? 'ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት' የሚሉት መጽሓፎችስ፡ ይህንኑ፡ የልጅሽንና የአንቺን መልእክት፡ በእኔ ተላላኪነት፡ ለእኒሁ ልጆችሽና ለሌላውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ያስተላለፍሽባቸው ጦማሮችሽ አይደሉምን? የቅርቡ፡ "ምሥራች!" የሚለው መልእክት የተላለፈበት ዕትምስ፡ የኹሉ ፈጣሪ የኾነው ልጅሽ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ሦስት ዓመት፡ በአንቺ ማንነት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያስገኘውን፡ የመጨረሻውንና ዘለዓለማዊዉን የብቅዓት ጸጋና ሕይወት፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ያቀዳጀ መኾኑን፡ የሚያበሥርና የሚያሳውቅ መጽሓፍ አይደለምን?

“ትውልዱ፡ በቃልና በእነዚህ ድርሰቶች አማካይነት የተላለፈለትን፡ ይህን፡ የአንቺንና የልጅሽን መልእክት፡ መስማቱና መቀበሉ፥ መፈጸሙም ቀርቶ፡ ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው ብቻ ሳይኾን፡ ከቤተ ክህነቱ ጭምር፡ በእነዚህ መጻሕፍት ላይ፡ በግልጽና በሥውር እየተካኼደ ያለውን፡ ረቂቅና ግዙፍ የተቃውሞ ዘመቻ፡ ልጅሽም፥ አንቺም፡ የምታውቁት አይደለምን? ይህ ኹሉ እየኾነስ፡ እኔ፡ ይህንኑ ተልእኮዬን፡ መቼ አቋረጥሁ? አንቺም፥ ልጅሽም እስከጠራችሁኝና ለዚሁ ተልእኮዬ፡ በሕይወተ ሥጋ እቆይ ዘንድ እስከፈቀዳችሁልኝ ድረስ፡ እቀጥላለሁ እንጂ፡ አላቋርጥም፤ እውቀቴና ኃይሌ፥ መሪዬም በኾነው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በእሥር፥ በግዞትና በስደት እያለሁም፡ ይኸው፡ እስካኹን ያላቋረጥሁትን አገልግሎት እንደማላቆም፡ ለአንቺም፥ ለልጅሽም የተሠወረ አይደለም።

"ነገር ግን፡ ይህን ኹሉ አድርጌ፡ እንኳንስ፡ ባዕዳኑ፥ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድም፡ የሰሙኝ አልመሰለኝም፤ ወደፊትም የሚሰሙኝ አይመስለኝም፤ ስለዚህ፡ 'ለልጅሽ፡ የሚሣነው ስለሌለ፥ ለአንቺም፡ ኹሉን ማድረግ ይቻልሻልና፡ በዚች ጾመ ኢትዮጵያ፥ በዚችም፡ በሰላም ለኢትዮጵያ ጾም፡ እንደእኔ፡ እንዲህ፡ ከፊታችሁ ወድቀው የሚማልሉትን፡ የታማኞች አገልጋዮቻችሁን ተማሕጽኖ ተቀብላችሁ፡ ለታላቅ መከራና ሥቃይ ለተዳረገው፡ ለዚህ፡ የቃል ኪዳን ትውልዳችሁ፡ የሚሻለውን መፍትሔ አድርጉለት!' ከማለት በቀር፡ ምን እላለሁ?

"እመቤቴ፥ እምዬ ድንግል ማርያም ሆይ! እንግዴህ፡ የእናንተን መፍትሔ ብቻ ለሚጠብቀው፡ ለዚህ አቤቱታዬ፡ መንሥኤ የኾነኝ ጽኑ ችግር፡ ይህ ነው።" አልኳት፡ በዚያው በኅሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ።

እርሷም፡ "አንተ፡ ገና በገሃድ እንድታውቀው ስላልተደረገ፡ የሰሙህ ሳይመስልህ ቆይቷል እንጂ፡ ብዙዎች የሰሙህ አሉ፤ አኹንም ብዙዎች የሚሰሙህ አሉና፡ ኺድ! ያልኩህን መልእክት፡ እንደተለመደው አድርስላቸው! እስካኹን ያደረስኸው፥ አኹን የሰጠሁህና ወደፊት የምትቀበለውም መልእክት፡ የመንፈስ ቅዱስ ስለኾነ፡ ሳትፈራና ሳታፍር አድርስ! ልጄና እኔ፡ ከአንተ ጋር ነን!" አለችኝ።

ለእርሷ፡ የእሺታ መልሴን ከመስጠቴ በፊት፡ ጌታዬ አምላኬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቅድስት እናቱና በእኔ መካከል የተካኼደውን የቃል ምልልስ ይሰማ ኖሮ፡ በዚያው፡ በኅሊናዬ ውስጥ እንዳለሁ፡ እንዲህ አለኝ፦

"በእናቴ ሰውነትና በእኔ ትስብእት፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ በሚኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ ምሕረቴና ቸርነቴ፡ ከዚህ የኢትዮጵያ ትውልድ አይርቅም፤ ክህደቱና ዐመፁ፥ አመንዝራነቱም ስለተደራረበበት፡ ይህ ትውልድ፡ በሥጋውም፥ በነፍሱም፡ በረሃብና በጥማት፥ በእርዛትና በደዌ፥ በእሥራትና በስደት፥ በእርስ በርስ ፍጅትና እልቂት ይኸው ይሠቃያል።

"ይህ ኹሉ የኾነውና የሚኾነው፡ ትውልዱ፡ ከኃጢአቱ፡ በንስሓ ላለመመለስ፡ በእምቢተኝነቱና በልበ ደንዳናነቱ ከመጽናቱ የተነሣ ነው።

ደግሞም፡ ከትውልዱ፡ እያንዳንዱ፡ በግል፥ በጋራም፡ ኹላቸው፡ እናቴንና እኔን፡ የበለጠ እንዲያውቁን፥ ከፈተናውና ከመከራውም ተምረው፥ በእነዚሁም ተገሥፀው፡ በንስሓ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው፡፡

"እየደረሰባቸው ያለውን፡ ይህን ኹሉ ፈተናና መከራ፡ ለደኅንነታቸው እንዲበጃቸው አደርግላቸዋለሁና፡ የወሰንሁት፡ የኢትዮጵያ ቀን ደርሶ፡ የጊዜው ቸርነቴ እስኪገለጥ ድረስ፡ ካለፈው ኃጢኣታቸው ተጸጽተው፡ ንስሓ ከመግባትና በትዕግሥታቸው ከመጽናት በቀር፡ በሚደርስባቸው ፈተናና መከራ ተሠቅቀው፡ ከቃል ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው እንዳይነዋወጹ ንገራቸው፥ ምከራቸው፥ አስጠንቅቃቸው፥ ገሥፃቸውም፡፡

"'እናንት የኢትዮጵያ ልጆች' እያልሁ፡ የእናቴ ልጆች አድርጌ፡ በእርሷ ስም የምጠራው፡ ይህ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና አምልኮው፥ ምግባሩና ኑሮው ላይ፡ የክህደትንና የዓመፅን፥ የአመንዝራነትንም ኃጢኣት በመፈጸም፡ እንዲህ ቢያሳዝነኝም፡ በእርሷ ስም የምጠራቸውን፡ እርሱንና የሚኖርባትን ይህችን ምድር፡ ለእናቴ ርስት አድርጌ ሰጥቼ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ የጠበቅኋቸው፥ ወደፊትም፡ የምጠብቃቸው ለምን እንደኾነ፡ ለዚሁ ትውልድ አበክረህ ንገረው!

"ይኸውም፡ አባቶቼና እናቶቼ፡ ጠብቀው ስላኖሩት፥ የዛሬዎቹ ታማኞች አገልጋዮቼም፡ ተረክበው ስላጸኑት፡ በእኔና በእነርሱ መካከል ስላለው፡ ስለቅዱሱ ኪዳኔ ብዬ መኾኑን፥ እንዲሁም፡ ስለእናቴና ስለስሜ ስል መኾኑን አሳውቃቸው፡፡" አለኝ፡ በዚያው፡ በኅሊናዬ ውስጥ፡፡

የእናትና ልጁ ንግግር ማብቃቱን፡ በመንፈሴ እንደተረዳሁ፡ ለእርሱ፡ ለፈጣሪዬ፥ ለእመቤቴም፡ የእሺታ መልሴን፡ በዚያው በኅሊናዬ እንዳለሁ ከሰጠሁ በኋላ፡ ኹለንተናዬ፡ በልዩ ደስታና እርካታ ተውጦ፡ እንደመባነን አልሁ፤ እስከዚያች አፍታ ድረስ፡ ተከድነው የቆዩ ዓይኖቼን ገላልጬ፥ በግንባሬ ተደፍቼበት ከነበረው ስግደቴም፡ አንገቴን ቀና አድርጌ ተነሣሁ፡፡

ይገርማችኋል! ለካ፡ "በፍቅር ፍርሃት የለም!" የሚለው መለኮታዊው ቃል አይታበልም፤ በዚህ መልክ፡ ከአምላክና ከእናቱ ጋር፡ በኅሊናዬ ውስጥ፡ በመንፈስ መነጋገር ጀምሬ እስክፈጽም ድረስ፡ ከፍቅር ድፍረት በቀር፡ የፍርሃት ስሜት ጨርሶ አልነበረብኝም፡፡

ወገኖቼ ሆይ! ሰውን ስለሚመለከተው ስለ፫ኛው ወገን፡ አምላክና እናቱ፡ በተለይ፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ እንዳደርስ፡ በጎሊናዬ መድረክ ላይ የሰጡኝን፥ እኔም በመንፈስ ቅዱስ የተቀበልሁትን መልእክት እነሆ፡ ሰማችሁ።

ይህን መልእክቴን ከማጠቃለሌም በፊት፡ እንደገና፡ በአጽንዖት ልገልጽላችሁ፥ ላስገነዝባችሁም የሚያስፈልገኝ፡ አንድ ታላቅ ቁም ነገር አለኝ፤ ይህም፡ ከረቂቁ ስሕተት የምትድኑበት ነውና፡ በትክክል ተረድታችሁ ልትፈጽሙት ይገባችኋል፤ እርሱም፡ እስካኹን፡ ከእኔ የሰማችሁትን፡ "በጎሊናዬ መድረክ ላይ፡ ከአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና ከእናታችን ድንግል ማርያም ጋር፡ በመንፈስ ተገናኝቼ ተነጋገርሁ!" የሚለውን ቃሌን፡ በተሳሳተ፥ ወይም፡ በተዛባ መንገድ ወስዳችሁ እንዳትጎዱበት፡ የሚያስጠነቅቅና የሚያስገነዝብ ነው፤

አዎን! ይህ ነገር፡ በእኔ ላይ፡ አንዳች ድንቅና ብርቅ ድርጊት እንደተፈጸመ፥ ወይም፡ ከሰው ኹሉ ተለይቶ፡ ለእኔ ብቻ እንደተደረገልኝ አስቆጥሮ፡ እኔን፡ በንጽሕና፥ በቅድስና፡ ከእያንዳንዳችሁ የተሻልሁ፥ ወይም፡ የበለጥሁ፡ ልዩ ፍጡር የሚያስመስል ስሜትን፡ በውስጣችሁ እንዳይፈጥር የሚያሳስበው ጥብቅ አደራዬ ነው። ይህን በመሰለ ስሕተት ምክንያት፡ ግለሰቦችና ኅብረተሰብ፡ በክፉ የጥፋት ወጥመድ ውስጥ እየወደቁ፡ በአህጉርና በዓለም ላይ ከፍ ያለ ጉዳት፡ ተደጋግሞ ሲደርስ መኖሩ በይፋ ይታወቃል።

በዚህ ረገድ፡ እዚህ ላይ፡ በኹለት ገጹ፡ ለእያንዳንዳችሁ ላሳውቃችሁ የፈለግሁትን፡ የእግዚአብሔርን እውነት ልግለጽላችሁ፦ ይህም፡ በአንድ ወገን፡ ምናልባት፡ በእናንተ በኩል፡ ቸኩላችሁ፡ እኔን፡ ወደዚያ፡ የየራሳችሁ ፈጠራ ወደኾነው፡ የግምት ደረጃ አልቃችሁ እንድትመለከቱኝ የሚገፋፋውን የተሳሳተ ስሜት፡ በውስጣችሁ አሳድራችሁ ከኾነ፡ ያን ጠንቅ፡ ልታስወግዱት የሚገባ መኾኑን የሚያስገነዝባችሁ ነው፤ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በእኔ በኩል ተደርጎልኝ ለሰማችሁት፡ ለዚህ ቸርነት፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየግላችሁ፡ እየራሳችሁን ልታበቁ የምትችሉ መኾናችሁን አረጋግጦ የሚያሳምናችሁ እውነታ ነው።

እስኪ፡ በማስተዋል ትመለከቱት ዘንድ፡ ይህን እውነታ፡ በበለጠ ላብራራላችሁ!

ከመግለጫዬ መግቢያ ላይ እንዳመለከትኳችሁ፡ በእናንተና በእኔ መካከል፡ ከቶ ምን ልዩነት፥ ምንስ መበላለጥ አለ? ምንም የለም፤ እናንተም፥ እኔም፡ ያው በአንዱ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርን፡ አንድ ዓይነት ሰዎች ነን፤ ፈጣሪ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ለእናንተም፥ ለእኔም፡ ያበረከተው ቸርነትና ያደረገው ምሕረት፥ የፈጸመው ፍቅርና የሰጠው ጸጋ፡ እኩልና አንድ ዓይነት ነው፤ በመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ፡ በመልከ ጼዴቅ የተረጋገጠውና በመጨረሻው ኢትዮጵያዊ መልከ ጼዴቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሕያውነት ለዘለዓለም የጸናው፡ የሦስቱ ጸጋዎች በረከት፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ባለቤትነት፡ እኩል፡ የእናንተም፥ የእኔም ነው።

እግዚአብሔር፡ በውስጣችን፡ አብሮን ኗሪና ሕያው ኾኖ፡ እያንዳንዳችንን፡ ያለማቋረጥ የሚያነጋግርበት ኅሊናም፡ ያው፡ በእናንተም፥ በእኔም ውስጥ ያለው፡ አንድ ነው፤ በየኅሊናችን አማካይነት፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪያችን ጋር ለመገናኘት የሚያስችለንንና የእርሱ ልጆች ለመኾን የበቃንበትንም፡ መንፈስ ቅዱስን፡ እናንተም፥ እኔም፡ ገና፡ ከሕፃንነት የክርስትና ጥምቀታችን አፍታ ጀምረን፡ ለብሰነው እንገኛለን:: አንድን ሰብአዊ ፍጡር፡ ለኢትዮጵያዊነት የሚያበቁት፡ እነኚህ የክብር ሀብታት ኹሉ፡ የእኔ ብቻ ሳይኾኑ፡ የእናንተም ናቸው::

እርግጥ፡ በእናንተና በእኔ መካከል፡ ልዩነትና መበላለጥ ሊኖር ይችል ይኾናል፤ ያም ልዩነትና መበላለጥ፡ ቀደም ብዬ እንደጠቀስሁት፡ ሰው ያመጣውና የሠራው እንጂ፡ እግዚአብሔር ያደረገውና የፈቀደው አይደለም፤ ይህም፡ ፈጣሪ፡ ለሰው ልጆች፡ ያለአድልዎና ያለልዩነት፡ ለኹሉም የሰጠውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፡ በእውነት ተቀብሎ፡ በእውነተኛ ምግባር፡ ለንስሓ ፍሬ በማብቃቱ ረገድ፡ እያንዳንዳችን፡ በተፈጥሮ ባገኘነው፡ የመምረጥ ነጻነታችንና የመወሰን ሥልጣናችን፡ ከየራሳችን የምናመነጨው፡ የፍላጎት ዓይነትና የፈቃደኝነት መጠን፡ ሊለያይና ሊበላለጥ የመቻሉ ነገር ነው::

እንግዴህ፡ ፈጣሪያችንን፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምን፡ እኔ ያነጋገርኳቸው፡ ለንስሓ ፍሬ በበቃው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር ኾኜ፡ እናንተም÷ እኔም፡ ባለን፡ የኅሊና መድረክና የመንፈስ መገናኛ እንጂ፡ በሌላ፡ ልዩ ምሥጢራዊ ዘዴ ወይም ብቅዓት አይደለም።

ለዚህ ነው፡ ለእኔ በኾነው በዚህ ነገር፡ አንዳች፡ ድንቅና ልዩ ተአምር እንደደረሰ አድርጋችሁ ለትገረሙ አያስፈልግም ያልሁት። በእናንተ፡ በእያንዳንዳችሁ ዘንድ፡ በእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አምልኮና ንስሓ የቀረበ፡ ፍጹም ፍላጎትና ፈቃደኛነት ካለ፡ ይህን የመሰለው ንግግር፡ በየኅሊናችሁ መድረክና በመንፈስ መገናኛችሁ አማካይነት፡ በአንድ ወገን፡ በፈጣሪና በቅድስት እናቱ÷ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በእናንተ መካከል፡ በየምክንያቱና በየጊዜው ብቻ ሳይኾን፡ ዘወትር÷ በየአፍታውም ሊካኼድ ይቻላል።

ይህ ቸርነት፡ ለእኛ ብቻ ሳይኾን፡ ለዚህ ሃይማኖታዊ አምልኮና ምግባራዊ ንስሓ ለሚበቃ፡ ለማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር ጭምር የተደረገ መኾኑን ስናስበው፡ ፈጣሪያችን፡ ለሰው ልጆች ኹሉ የለገሠው ጸጋው፡ እስከዚህ ለፍጹምነት የደረሰ በመኾኑ፡ አዎን! የልግሥናው መጠን፡ ልብን፡ በፍቅር ያጥለቀልቃል።

ከዚህ ጋር፡ ልትገነዘቡት የሚገባ፡ ሌላ ቊም ነገር ስላለ፡ ያን ደግሞ፡ ላመልክታችሁ! እርሱም፡ ይህን መግለጫ በምትመለከቱበት ጊዜ፡ የአገልግሎታችን፡ አንዱ መሠረታዊ ዓላማ የኾነውን ተግባር፡ በአእምሮአችሁ ውስጥ፡ ያለማቋረጥ እንድታዘክሩት የሚያስፈልጋችሁ መኾኑን ነው፤ ይህ፡ የአገልግሎታችን፡ አንዱ መሠረታዊ ዓላማም፡ በዲያብሎስ ሓሰት የተጥለቀለቀውንና በተከታዮቹ ሰዎች ድርጊት የማሰነውን የኢትዮጵያ ትውልድና የዓለሙን ኅብረተሰብ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በአገልጋዮቿ ገድል ማስተካከልና አጥድቶ ማዘጋጀት÷ ለመልካሚ ሕይወትም ማብቃት ነው።

በዚህ መልክ፡ የጾመ ኢትዮጵያና የሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ጥሪዎች ያስገኙትን ምላሽ፡ በትክክለኛው የጻኝነት ዓይን እየተመለከቱ ሲያመዛዝኑት፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደታተተው፡ በአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና በእናታችን ድንግል ማርያም የተነገረው ቃልና የተሰጠው መልእክት፡ እውንና ተጨባጭ መኾኑን፡ የየራሳችሁ ኅሊና፡ በመንፈስ ቅዱስ ያረጋግጥላችኋል፤ ከዚያ በላይ ደግሞ፡ እስኪ፡ እናንተም፥ እኔም፡ የምናውቀውንና በገሃድ ያየነውን፡ የምስክርነት ቃላችንን እንስጥ!

በኢትዮጵያ ከሚኖረውና ከኢትዮጵያ ውጭ፡ በዓለሙ ኹሉ ከተበተነው ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት መካከል፡ ይህን፡ የጾመ ኢትዮጵያንና የሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ጥሪዎችን የሰማው፥ መልእክቱም የደረሰው ስንቱ ነው? ከሰማውና ከደረሰው መካከልስ፥ በተደላደለ ኑሮና በምቾች ካለው ብቻ ሳይኾን፥ በይበልጥ፡ በችግርና በሥቃይ፥ በእሥራትና በስደት፥ በተለያየ ፈተናና መከራ ውስጥ ከሚገኘው ጭምር፡ ጥሪዎቹን የተቀበለው፥ መልእክቶቹንም የፈጸመው ስንቱ ነው?

እንግዲህ፡ የጾሞቹና የምሕላዎቹ ውጤታማነትና ፍሬያማነት የሚመጠነውና የሚመዘነው፡ የጥሪዎቹና የመልእክቶቹ ዓላማና ተግባር፡ በእያንዳንዱ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው ግለሰብ ዘንድ፡ ባገኘው እውነተኛ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት መኾኑ ግልጽ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ "ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ እንድንሰጥ፡ በቅድሚያ የምንጠየቅ፡ እያንዳንዳችን ነን" የሚለውን ቊርጥ የአዎንታ ቃል፡ ልንቀበለው፡ ተገቢ ይኾናል፤ በየራሳችን የኾነውንና የፈጸምነውን፡ እያንዳንዳችን እናውቀዋለንና።

በዚህ ረገድ፡ የእኔን፥ የበኩሌን ድርሻ፡ ከላይ ዘርዝሬ ባቀረብሁት ሐተታዬ፡ የተወጣሁት ይመስለኛል። እስኪ፡ አኹን ደግሞ፡ ለአንዲት አፍታ፡ ወደእናንተ መለስ ልበልና፡ ልጠይቃችሁ?

እነዚህኑ፡ ጾመ ኢትዮጵያንና የሰላም ለኢትዮጵያ ጾምን በሚመለከት፡ የእናንተስ ኅሊና ምን አላችሁ? ምንስ እያላችሁ ነው?

መቼም፡ በእያንዳንዳችንና በኹላችንም ዘንድ የተገኘውን ውጤትና ፍሬያማነት፡ መንፈሳችን፡ ለየራሳችን ከሚነግረን በላይ፡ እናትና ልጇም፡ በመንፈስ ቅዱስ ያውቁታል፤ አዎን! ስላወቁትማ፡ ያን መልእክት እንዳደርስላቸው፡ በኀሊናዬ መድረክ ላይ ትእዛዛቸውን ሰጡኝ።

እንደእውነተኞቹ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት እምነት፡ የዘመኑ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ፈጣሪውንና የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን እናት አገሩን፡ ኢትዮጵያን ትቶ፥ የራሱ የኾነውንም እምነትና ሥርዓት ንቆ፡ ለባዕዳንና የእነርሱ ለኾነው እምነታቸውና ሥርዓታቸው መገዛትን ስለመረጠ፥ ከዚህ ኃጢኣቱም፡ 'በንስሓ አልመለስም!' ብሎ፡ በክህደቱ፥ በዓመፁና በአመንዝራነቱ በመቀጠሉ፡ ይህንኑ ትውልድ ሊቀጣ፡ ቀደም ብሎ፡ የደርግ የግፍ አገዛዝ ሠለጠነበት።

ደርግ፡ ይህንኑ ግዳጁን ፈጽሞ ሲያበቃ፡ እርሱ ተወግዶ፡ "ኢሕአዴግ" የተባለው፡ የአኹኑ አገዛዝ ደግሞ የተተካው፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ይኸው ትውልድ፡ አኹንም፡ ከኃጢኣቱ፡ "በንስሓ አልመለስም!" ብሎ፡ በእምቢተኝነቱና በልበ ደንዳናነቱ ስለቀጠለ፡ ይህንኑ ባተሌ ትውልድ፡ በረቀቀ ጭካኔ፡ የሥራውን ዋጋ እንዲከፍል መኾኑ፡ መታወቅ አለበት።

ታዲያ! ጾመ ኢትዮጵያንና የሰላም ለኢትዮጵያ ጾምን በሚመለከት፡ በአገር ውስጥ በሚገኘውና ከአገር ውጪ በተበተነው የኢትዮጵያ ትውልድ ዘንድ፡ የኾነውና የታየው፥ ዛሬም እየኾነና እየታየ ያለው ኹኔታ፡ በአጠቃላይ፡ ይህን የሚመስል ከኾነ፡ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እመቤታችንና እናታችን ድንግል ማርያምም፡ ለዚህ ትውልዳቸው እንዳደርስላቸው፡ በኀሊናዬ በኩል፡ በመንፈስ ቅዱስ ያዘዙኝን፡ የዚህን፡ የአኹኑን መልእክት እውንነትና አግባብነት የሚያጠያይቅ፡ አንዳች አጠራጣሪ ነገር ሊኖር፡ ከቶ ይችላልን? አይችልም።

ስለዚህ፡ የእነርሱ ታማኞች ልጆቻቸውና አገልጋዮቻቸው ለኾናችሁት ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ ይህን እላለሁ፡-

እየራሳችሁን ብቻ ሳይኾን፡ አገራችንን ኢትዮጵያንና ወገናችን የኾነውን፡ ይህን ትውልዷን፥ በአጠቃላይም፡ መላውን የዓለም ሕዝብ ለማዳን፡ ቍጥራችሁ፡ አንሶ፡ አሥርም ብትኾኑ እንኳ፡ ለቸሩ ፈጣሪያችን የብዛት ውሳኔ፡ ትበቃላችሁና፡ ይህን፡ የእናትና ልጇን የምሥራች መልእክት፡ በተለመደው ሃይማኖታዊ ታማኝነታችሁ ተቀብላችሁ፡ በተለመደው ምግባራዊ ንስሓችሁ፡ ለመልካሙ ጣፋጭ ፍሬ እንድታበቁት አደራ እላችኋለሁ፡፡

በዚህ ገድላችን፡ የኢትዮጵያ አምላክና ቅድስት እናቱ፡ ምንጊዜም፡ በያለንበት፡ በመንፈስ ቅዱስ አብረውን ናቸውና፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንና ምግባራችን፡ እስከመጨረሻው የጸናን እንኹን! አሜን፡፡

\+ + + + + + +